ከአይሁዶች ጋር የሚደረገውን ትግልና ጦርነት በአረብ ብሔረተኝነት ስም ለማድረግ መጣራቸው በኢስላም፣ በሙስሊሞችና በዓለስጢም ጉዳይ ላይ የተፈፀመ ከሀዲት ነው። በኢስላም ስም ለኢስላም መሆን ያለበትን ትግል በአረብ ብሔርተኝነት ወደሚደረግ ትግል በመለወጣቸው በኢስላም ላይ ከሀዲት ፈፅመዋል። ኢስላማዊ ወንድማማችነትን ወደ አረብ ወንድማማችነት በመለወጣቸው ምክንያት ሙስሊሞችን ከደዋል። ኃያሉ አምላካችን አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ إِخْوَةٌ فَأَصْلِحُوا۟ بَيْنَ أَخَوَيْكُمْ ۚ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ ﴿١٠﴾ ﴾
الحجرات: ١٠

"ምእመናናት ወንድማማቾች ናቸው፣ በሁለት ወንድሞቻችሁም መካከል አስታርቁ፣ ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህን ፍሩ።" (አል-ሑጁራት፡ 10)

﴿ إِنَّ هَٰذِهِۦٓ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَٰحِدَةً وَأَنَا۠ رَبُّكُمْ فَٱعْبُدُونِ ﴿٩٢﴾ ﴾
الأنبياء: ٩٢

"ይህች (ሐገጋት) እንዲት መንገድ ስትሆን በእርግጥ ሃይማኖታችሁ ናት፣ እኔም ጌታችሁ ነኝና ተገዙኝ።" (አል-አንቢያእ፡ 92)

የተጠቀሱት ሁለቱም አንቀፆች የሚናገሩት በሙስሊሞች መካከል ስላለው ዕውነተኛ ግንኙነት– ስለ-ኢስላም ነው። ኢስላም ይህን ግንኙነት ከደም፣ ከዘር፣ ከቀለም፣ ከድንቋ ወይም ከታሪክ ግንኙነት በላይ መርጦታል፣ ከሁሉም በላይ አስበልጦታል።

በሙስሊሞች ታሪክ ውስጥ ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ሌላ ከሀዲት ታይቶ ያውቃልን?

ሙስሊሞች ከጠላቶቻቸው ጋር ባኪሒዲቸው ጦርነቶች ውስጥ ከዚህ ከሀዲት ጋር የሚመሳሰል ኢስላማዊ ወንድማማችነት የተስተባበለበት ሌላ ከሀዲት ተሰምቶ ያውቃልን?

ከላይ እንደተነጋገርነው በኢስላምና በሙስሊሞች ላይ የተፈፀመ ከሀዲት ብቻ ሳይሆን በዓለስጢማዊያን ጉዳይ ላይ የተፈፀመ ከሀዲትም ነው፣ ምክንያቱም በአረብ ብሔርተኝነት ስም ወደ መታገል ጥሪ የሚያደርጉ ወገኖች አረብ ያልሆኑ ሙስሊሞች በሙሉ ከአጀንዳው እንዲርቁ፣ ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ አጀንዳውን ከአረቦች ጋር ብቻ

ሊያይዘው እንዲያስቡ ወይም የተቀረው ሙስሊም ዓለም የኢኔ ንዲ ሊይደለም እንዲል አድርገዋል። ከኢስላም ይልቅ በአረብ ብሔርተኝነት ስም መታገልን በመረጡና ለሌሎች ጥሪ በሚያደርጉ በእነዚህ መሾች ምክንያት በሙስሊሞች መካከል የመከፋፈል ስሜት ከተፈጠረ በኋላ ሁሉም ሙስሊም አንድነት እንዲፈጥር እና የተወረረ ቅዱስ መሬቱን ነፃ እንዲያወጣ መጠበቅ ተቀባይነት ይኖረዋልን?

ኧረ ለመሆኑ ሙስሊሞች አንፀባራቂ በሆነው ታሳት ታሪካቸው ውስጥ ከኢስላም፤ ከኢማን እና ከቁርአን ውጭ ሌላ የሚያሸናንፉ፤ ሌላ የሚያስተሳስራቸው ነገር ያውቃሉን?

እነዚህን ስንኞች የቋጠረ ገጣሚ እንዴት ዕውነት ብሏል!

ተጣሪው ከወገኖቹ ጎን ይገኛል ቁም

ከጎላው ክቡራን አንዱ መደረግን አልሞ

ሌሎች ሰዎች ሁሉ ሲኮሩ

ቀይስን ወይ ተሚምን እየጠሩ[20]

እኔ ግን የምጠራው ወገን የለኝም

በአርግጥ ከኢስላም ውጭ ሌላ አባት አላውቅም

ሸይኽ ሙሐመድ ኒምር አል-ኻዚብ፡ "አል-ኢማን ጦሪቴና አላ አን-ነስር" (ኢማን ወደ ድል የሚያደርሰን ጎዳና) በሚል ርዕስ በፃፉት መፅሃፋቸው ውስጥ የሚከተለውን ሃሳብ አስፍረዋል፡

የአረብ መሪዎች ለረጅም ጊዜ የፍልስጤማዊያንን ችግር ጥርት ያለ የአረቦች ጉዳይ አድርገው በማቅረብ ተጠምደው ኑረዋል። ከዚህ ጀርባ ያለውን ምክንያት በእውነት አላውቅም. . .

አረቦች ለምን ወደ ሰባት መቶ ሚሊዮን የሚጠጉ እጅግ ምርኖና ለም በሆኑ መሬቶች ላይ የሚኖሩ እና የነዳ እና የጥቁሩ ወርቅ ባለቤት የሆኑ ሌሎች ሙስሊሞችን ችላ እንዳሉ በእውነት አላውቅም።

---

[20] ቀይስ እና ተሚም ኢስላም በአረቢያ ምድር እንደ አዲስ ከመምጣቱ በፊት እጅግ የታወቁ ሁለት ጎሳዎች ነበሩ (ተርጓሚው)

ሁሉም ህዝቦች ከሊሎች ጋር ያላቸውን ወዳጅነት ለማጎልበት በሚጥሩበትና የእርዳታ እጃቸውን በሚዘረጉበት በዚህ ዘመን ለምን ይህን እንደሚያደርጉ በእውነት አላውቅም።

እኔ እንደገባኝ፣ ከዚህ ተግባራቸው እንደተረዳሁት፣ እነዚህ ሰዎች በአረቡ ዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ማስደሰት ይፈልጋሉ። ነገር ግን ይህ ጉዳይ ክርስቲያን ዜጎቻችንን የሚያስከፋ ነውን? ለወንድሞቻችን መድረሳችን፣ እየሱስ የተወለደባትን ቦታ እና በፍልስጤም ምድር የምትገኘውን መንድሞቻችን እየሱስ ሞቶ የተነሳባት ሥፍራ ናት ብለው የሚያምኑባትን ቤተክርስቲያን ነፃ ማውጣታችን ያስከፋቸዋልን? አረብ ያልሆኑ ሙስሊም ወንድሞቻችን ቅድስቲቷን መሬት ነፃ ለማውጣት መላተፋቸው ያስከፋቸዋልን?

ከዕዮናዊያን ጋር ከሚደረገው ትግል ጋር በተያያዘ በኢስላም እና በአረባዊነት መካከል ለሚታየው ልዩነት መነሻ ምክንያቱ ዛሬ በምንኖርበት ዓለም በንያማኖት ስም ጥሪ ማድረግ የማይደነት ወይም የማይታመንበት አካሔድ ነው ብለው ማሰባቸው ነው። ከዚህ በተጨማሪ የፍልስጤማዊያንን ጉዳይ የኢስላም ጉዳይ ካደረግነው ሊሎች በንላቀርነት ይከሰናል ብለው መስጋታቸው ነው። እዚህ ላይ ነያቂ ማንሳት ይኖርብናል፦ እስራኤል የተመሰረችውና እንደ ሃገር የቆመችው በንያማኖት መሠረት ላይ አይደለምን? በውጭው ዓለም የሚነዙት ፕሮፓጋንዳ በአይሁዳዊነት ስም አይደለምን? ዋናዘማን የተባለ አይሁድ ከሳፋቸው ትውስታዎቹ[21] ውስጥ የሚከተለው ይገኝበታል፦

> የብሪታኒያን የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ለርድ ባልፎርን (lord Balfour) አግኝተው እንዲህ ብሎ ጠይቆን ነበር፦ "አዲስቲን አገራችሁን የጋንዳ ውስጥ እንድትመሠርቱ የተረበላችሁን ሃሳብ ለምን አልተቀበላችሁም?" እኛም "ያለምንም ጥርጥር፣ ዕዮናዊነት ፖለቲካዊና ብሔራዊ ግቦችን ያንገበ እንቅስቃሴ ነው

ከዚህና ከዚህ በንላ ከዕዮናዊ መሪዎች የተወሰዱ ጥቅሶች በዕሁፉ ውስጥ ማሳተሚያቸው ስላልተፈቀደ እና ምንጫቸውንም ፈልጎ ማግኘት ስላልተቻለ፣ ከአረብኛ ትርጉማቸው የተተረጎሙ መሆናቸውን ለአንባቢያን ማስታወስ እንወዳለን (አዘጋጁ)

ይሁን እንጂ መንፈሳዊ ጎኑን ችላ ካልን ፖለቲካዊም ይሁን ብሔራዊ ህልሞችን ዕውን ማድግ በፍፁም አንችልም።" በማለት መለስኩለት።

ሔርዝል (Herzl) የተባለው አይሁዳዊ እ.ኤ.አ በ1897 በተካሔደው የቤዝል ኮንፈረንስ (Basel Conference) ላይ ተገኝቶ፦ "ወደ ፅዮናዊነት መመለስ ወደ አይሁዳዊነት መመለስን ተከትሎ መምጣት አለበት።" የሚል ሃሳብ ሰንዝሮ ነበር።

ቤንጉሪዮን (Bengurion) ለፕሬዝዳንት ዲጋውሌ (De Gaulle) ዕፎት በነበረው ደብዳቤ ይህን ነግሮት ነበር፦ "ባቢሎናዊያን እና በሮማዊያን ከደረሰብን ሁለት ትላልቅ ሽንፈቶች በኋላ እና ለሰንድ ሺህ ዓመታት ያህል ክርስቲያኖች በእኛ ላይ ካዳበሩት ሥር የሰደደ ጥላቻ ተርፈን በሕይወት መገኘት የቻልንበት ሚስጥር የሚገኘው በቅዱስ መፅሐፉ ላይ ባለን መንፈሳዊ ዕምነት ነው።"

የአይሁድ መሪዎች እያንዳንዱ አይሁድ ይህን ቃልኪዳን እንዲገባ አውጀዋል፦ "ኦ! እስራኤል፣ ይኸው ቃል ኪዳኔ፣ ለጌታ፣ ለተውራህ፣ ለአይሁድ ህዝብ እና ለአይሁዳዊት አገር ታማኝ ለመሆን ቃል እገባለሁ።"

ለዓለም አቀፋዊ ፅዮናዊነት በተደረገው ሃያ አምስተኛ ኮንፈረንስ ላይ (25 December 1960) ደግሞ ቤን ጉሪዮን የሚከተለውን ተናግሮ ነበር፦ "እያንዳንዱ አይሁድ ወደ እስራኤል መሰደድ አለበት። እስራኤል ከተፈጠረች በኋላ ከእስራኤል ውጭ የሚኖር እያንዳንዱ አይሁድ ከተውራህ አስተምህሮ እያፈነገጠ መሆኑ እና በየቀኑ በአይሁድ እምነት እየጎደ መሆኑ ሊነገረው ይገባል።"

በመንፈሳዊ እሴቶች ግፊት የአይሁድ ህዝብ የደረሰበትን ደረጃ የሚከተሉት ነጥቦች በጨረፍታም ቢሆን የሚያሳዩ ይመስለኛል፦

- የሃገራቱ መጠሪያ ስም እስራኤል ተባለ።
- ቅዳሜ ቀን ሲሰራ የተገኘ ማንኛውም ሰው ይወገራል።
- ሲቪል ጋብቻዎች በሃገራቱ እውቅና አያገኙም ወይም ዕውቅና አይሰጣቸውም።

- በአይሁድ ዕምነት የማይፈቀድ ምግብ የሚያዘጋጁ ሬስቶራንቶች ይዘጋሉ።
- እያንዳንዱ አይሁድ መጠሪያ ስሙን ከተውራህ መምረጥ አለበት።

ከአሞር ጊዜ በኃላ ነሲም-በእስራኤል ውስጥ ትልቁ 'ራቢ'- ታልሙድ የእስራኤል ህግ እንዲሆን ፊልጎ ነበር። ከርሱ በፊት የነበረኛዋ አገር የማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስትር ተውራህን የእስራኤል የመሆን እውቅና እንዲያገኝ ለማድረግ ጥረት አድርጎ ነበር።

የሰማነው የመጨረሻ ዜና እንደሚገልፀው፤ በአይሁድ ኃይማኖት መሠረት ሌት ልጅ የኃይል ልጅሙን መያዝ (መራ መሆን) አይፈቀድላትም የሚለውን አስተምህሮ ምክንያት በማድረግ ትልቁ ፓርቲ ለእስራኤል ጠቅላይ ሚንስትር ጎልዳ ማይር (Golda Meir) ድምፅ ነፍጎታል የሚል ነበር።[22]

ጠላቶቻችን በኃይማኖት ስም መራታችንን እንዲቀሙ፤ በኃይማኖት ስም አንድነት እንዲፈጥሩ እና ኃይማኖት መሠረት ያደረገ ግዛት እንዲመሠርቱ መተው፤ በተቃራኒው እኛ ወደ ዓለም ዕውነት ጋባጮቹ፤ እኛ ቀኖተኛ የጉዳዩ ባለቤቶች፤ በወላኝ ጦርነታችን ውስጥ የአላህ ህግ የሆነውን ኢስላምን ለማሳተፍ ማፈራችን፤ ሳልታ ለማስገባት መሸማቀቃችን፤ ከቀንደኛ ጠላታችን ጋር የምናደርገውን ትግል በምንሞርለት እና በምንሞትለት እስልምናችን ስም አለመመራታችን ዕውነት የጤና ነው? ምክንያታዊ ወይም ፍትሃዊ ነው? ከዚህ ሁሉ በኃላ የፍልስጤማዊያን ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች ጉዳዩን የአረቦች ብቻ አድርገው ሰባት መቶ ሚሊዮን አረብ ያልሆኑ መስሊሞችን ችላ ብለው መተዋቸው በምን ሊተነተን ይችላል?

በአረብ ብሔርተኝነት ስም የሚዋጉ መስሊሞች ከጠላት አንዳች ነገር ለማግኘት ማሰባቸው ወይም በወላኝ ትግል የአላህን እገዛ መጠበቃቸው ተቀባይነት አለውን?

---

[22] አል-ሐዋዲስ መፅሔት, ቅፅ ቁ 587, ፌብርዋሪ 1968

የፍልስጤማውያኑ የትላንት እና የዛሬ ትግል በንፅፅር ሲታይ ባጭሩ ይህን ይመስላል። ሚዛናዊ አዕምሮ ያላቸው ሰዎች ሊያስተውሉት፣ ሊማሩበት፣ ቅድስቲቷን ምድር ከአይሁዶች መዳፍ ፈልቅቀው ነፃ ለማውጣት እና በተስፋ የሚጠበቀውን ድል ለማሳካት ይችሉ ዘንድ የተሻለውን መንገድ መርጠው ሊጓዙበት ይችላሉ ብዬ አስባለሁ። ይህ የሚሆነው ግን የራሳቸውም ሆነ የሚመጣው ትውልድ የሚመጥነውን ክብር እንዲያገኝ የማድረግ ፍላጎቱ ካላቸው ብቻ ነው።

መድህን የሚገኝበት እና ክብር የሚመለስበት ብቸኛው መንገድ ኢስላም ነው፣ ወደ ድል መዳረሻው ጎዳናም እሱው ነው፦

﴿ وَقَالَ ٱلَّذِى ٱشْتَرَىٰهُ مِن مِّصْرَ لِٱمْرَأَتِهِۦٓ أَكْرِمِى مَثْوَىٰهُ عَسَىٰٓ أَن يَنفَعَنَآ أَوْ نَتَّخِذَهُۥ وَلَدًا ۚ وَكَذَٰلِكَ مَكَّنَّا لِيُوسُفَ فِى ٱلْأَرْضِ وَلِنُعَلِّمَهُۥ مِن تَأْوِيلِ ٱلْأَحَادِيثِ ۚ وَٱللَّهُ غَالِبٌ عَلَىٰٓ أَمْرِهِۦ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٢١﴾ ﴾ يوسف: ٢١

"ያም ከምስር የገዛው ሰው፣ ሰሚስቱ «መኖሪያውን አክብሬ ሲወቅመን ወይም ልጅ አድርገን ልንይዘው ይከጀላልና፤» አላት፣ እንደዚሁም ለዩሱፍ (ገዥ ልናደርገውና) የሕልሞችንም ፍች፣ ልናስተምረው በምድር ላይ አስመቸነው፣ አላህም በነገሩ ላይ አሸናፊ ነው፣ ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያውቁም።" (ዩሱፍ፡ 21)